# የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ አጠቃላይ ትንተና

በባለፈው ጽሁፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ከቅጽ ሐ የቀሩትን የዳሰስን ሲሆን በዚህ ጽሑፍ ቅጽ ‹መ› ን በዝርዝር ለመዳሰስ እንሞክራለን።

## ቅጽ መ፡ የግብይት ደንቦች

ቅጽመ የደንበኛ ግንኙነቶች የቁጥጥር ሂደት በተመለከተ ሰፊ ድንጋጌዎችን ይዟል። የደንበኛዎን ይወቁ መስፈርቶች ጋር በተያያዘ የግብይት አባላት እውነተኛ የደንበኛ ማንነትና መረጃ በየጊዜው መዝግበው እንዲይዙ፣ የግብይት አባላት ገበያው በየጊዜው የሚያወጣውን ስጋት ይፋ የማድረጊያ ሰነድ ለደንበኞች በመስጠት ደንበኞች ከሚሰሩት ስራ አንፃር ስጋታቸውን እንዲመረምሩ እና ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ፣ ደንበኞች ስላሏቸው መብትና ግዴታ እንዲያውቁ ማድረግ፣ የግብይት አባላት ከሚሰሩት ስራ እና የግብይት ሞዴል ከደንበኞቻቸው ስጋት ጋር በማናበብ መውሰድ የሚገባቸውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እና የግብይት አባላት የእያንዳንዱን ደንበኛ ስጋት ይፋ የማድረጊያ ሰነድ አስፈርሞ እንዲይዝ ያዛል። እነዚህ ድንጋጌዎች በህገ ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብን ወንጀል የመከላከል ቅድመ ጥንቃቄ መስፈርቶች ሲሆኑ የግብይት አባላትተግባራዊነታቸውን በማረጋገጥ ረገድ እነዚህ ጉዳዮች ሊያስከትሉ የሚችሏቸውን አደጋዎች ደንበኞች እንዲረዱ ማድረግ አለባቸው።

የደንበኛሂሳቦች ቁጥጥር የግብይት አባላት የሂሳብ መክፈቻ፣ መዝጊያ እና የግብይት ቁጥጥርን የሚሸፍኑ የጽሁፍ ፖሊሲዎችን እንዲይዙ ያዛል። ሂሳብ መክፈትን የሚያፀድቁ ሰራተኞች ፈቃድ ያላቸው ተሿሚ እንደራሴዎች ሲሆኑ የደንበኞችን የፋይናንስ ሁኔታ፣ ዓላማዎች እና አደጋ የመቋቋም አቅምን መረዳት የሚችሉ መሆን አለባቸው።

ሌላው በቅጽ መ የተመለከተው የደንበኛ ትዕዛዝ ማረጋገጫ ሥነ ሥርዓት ሲሆን የግብይት አባላት የደንበኛ መመሪያዎችን እንዴት እንደሚቀበሉ እና እንደሚፈጽሙ ያመላክታሉ። በዚህ ሥነ-ሥርዓት የግብይት አባሉ አስቀድመው የተፈረሙ ባዶ ትዕዛዞች ወይም የመመሪያ ሰነዶች ከደንበኛው መቀበል የተከለከለ ነው። ይህም ደንበኞችን ካልተፈቀደ ግብይት የሚጠብቅ ድንጋጌ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለግብይት አባሉ የተሰጡ የግዥ ወይም የሽያጭ(የግብይት) ትዕዛዞች በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ተሞክሮ መፈፀም ካልተቻለ በደንበኛው መታደስ አለባቸው። ይህም የቆዩ ትዕዛዞች ተገቢ ያልሆኑ አፈፃፀሞችን እንዳያስከትሉ ይከላከላል።

ሌላው በዚህ ቅጽ የተካተተው የደንበኛ ጥበቃ ሥርዓት ዋንኛ መሳሪያ የሆነው የግብይት አባሉ የደንበኞችን ሂሳብ ለያይቶ መያዝ ነው። የደንበኛ ገንዘቦች በግልጽ እንደ ደንበኛ መለያዎች በተሰየሙ የተለያዩ የባንክ ሂሳቦች ውስጥ መቀመጥ እንዲሁም ለዚህ ተፈፃሚነት ይረዳ ዘንድ የግብይት አባሉ በደንበኞች ሂሳብ ውስጥ ገንዘብ ስለማስገባት እና ስለማውጣት በሚመለከት በገበያው እና በራሳቸው የወጡ ደንቦችን ማክበር አለበት። የደንበኛ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በተመሳሳይ መልኩ ከግብይት አባሉ የባለቤትነት ንብረቶች ወይም ሂሳቦች ተለይተው መያዝ አለባቸው። እነዚህ የመለያየት መስፈርቶች የግብይት አባሉ ኪሳራ ቢደርስበትም እንኳን የደንበኞችን ሀብቶች የማይነኩ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።

## የግብይት ሥነ-ምግባርእናምርጥአፈፃፀም

የቅጽ መ ምዕራፍ 4 ምርጡን የአፈፃፀም መርህ ያስቀምጣል። በዚህ መርህ የግብይት አባላት የደንበኛ ትዕዛዞችን ሲፈጽሙ ደንበኞች ምርጡን ውጤት እንዲያገኙ መሆን አለበት። ይህ መርህ ዋጋን፣ ወጪዎችን፣ ፍጥነትን፣ የአፈጻጸም እድልን እና ሌሎች ነገሮችን ግምት ውስጥ ያስገባል። የግብይት አባላት የትዕዛዝ አፈፃፀም ፖሊሲዎችን ማውጣት እና መተግበር፣ ውጤታማነታቸውን መከታተል እና ለደንበኞች መረጃ መስጠት አለባቸው።

የትዕዛዝአያያዝ ድንጋጌዎች የግብይት አባላት የደንበኛ መመሪያዎችን እንዴት እንደሚያስተዳድሩ የሚመለከቱ ናቸው። ትዕዛዞች በፍጥነት እና በትክክል መመዝገብ፣ በፍትሃዊነት መመደብ እና በደንበኛ መመሪያ መሠረት መፈጸም አለባቸው። የግብይት አባሉ የደንበኛ ትዕዛዞችን ከራሱ ከባለቤትነት ግብይቶች ጋር ማዋሃድ መከልከል የግብይት አባላት የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የደንበኛ ትዕዛዞችን እንዳይጠቀሙ ያግዳቸዋል።

# የስህተትግብይቶች

ምዕራፍ 5 ሊከሰቱ ስለሚችሉ የስህተት ግብይቶች ይደነግጋል። የግብይት አባላት ከደንበኞቻቸው የተረጋገጠ ትዕዛዝ ከተቀበሉ በኋላ ወደ ግብይት ሥርዓቱ ለሚያስገቧቸው ትዕዛዞች ትክክለኛነት ብቸኛ ሃላፊነት ያለባቸው ሲሆን በዋና መዝገቦቻቸው ውስጥ በስህተት የሚፈጠሩ ግብይቶችን በስህተት ሂሳቦች መዝግበው የመያዝ ኃላፊነት አለባቸው። የግብይት አባላት በዚህ መልኩ በዋና መዝገባቸው ውስጥ የስህተት ግብይት መዝገብ መያዝ ካልቻሉ የገበያውን የግብይት ሥነ-ሥርኣት መጠቀምም ሆነ ግብይቶችን መፈጸም የተከለከለ ነው።

ግልጽ በሆኑ ስህተቶች አስተዳደር አሰራር መሰረት እነዚህ የስህተት ግብይቶች በ30 ደቂቃዎች ውስጥ ለገበያው ሪፖርት ሲደረጉ እና የተቃራኒ ወገን ፈቃድ ጨምሮ የተወሰኑ መስፈርቶችን ሲያሟሉ የግብይት ስረዛን ወይም ማስተካከያ ይፈቀዳል።ግልጽ የሆኑ ስህተቶች ምድቦች የምንላቸው ግብይቱ የመነጨው የአንድን ሰነድ ሙዓለ ንዋይ በገበያው ካለው መጠን አንጻር ከገበያው ዋጋ በተጋነነ መልኩ በሚጨምር የመግዣ ወይም የመሸጫ ዋጋ ጥያቄ ላይ ተመስርቶ የተፈጸመ ሲሆን፣ የአንድ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ሲጀመር የነበረው ዋጋ

ሲጠናቀቅ ከነበረው ዋጋ አንጻር በተጋነነ ዋጋ መግዛት ወይም መሸጥ እና ይህንን ዋጋ ሊያስረዳ የሚችል አሳማኝ ውጫዊ መረጃ ሳይኖር ሲቀር፣ በማንኛውም መልኩ ከገበያው ዋጋ በተጋነነ ዋጋ ምክንያት፣ በተሳሳተ የሂሳብ ቁጥር ምክንያት እና ሌሎች መሰሎች ናቸው።የገበያው መተዳደሪያ ደንብ እንደነዚህ ያሉ የግብይት ስህተቶች ሲፈጠሩ በአሰራር ለመፍታት ግልጽ የሆኑ ሥነ-ሥርዓቶችን በማቅረብ ስህተቶች አንዳንድ ጊዜ ሊከሰቱ እንደሚችሉ እውቅና በመስጠት የገበያውን ተዓማኒነት ይጠብቃል።

# የተከለከሉ ተግባራት

የደንቡ ቅጽ መ ምዕራፍ 6 በጥብቅየተከለከሉ እንቅስቃሴዎችን ይዘረዝራል። ማንኛውም የግብይት አባል ለደንበኛው ትርፍ እንደሚያስገኝ ወይም ኪሳራ እንደማይደርስባቸው ማረጋገጫ መስጠት የተከለከለ ነው። ይህክልከላ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች አሰራር ውስጣዊ አደጋን እንደሚያካትቱ እና ደንበኛው ትርፍ እንደሚያገኝ ወይም ኪሳራ እንደማይደርስበት በግብይት አባላት የሚሰጥ የተስፋ ቃል በተለምዶ አሳሳች ወይም አጭበርባሪ መሆኑን የሚያንፀባርቅ ነው።

ሌላው በገበያው መተዳደሪያ ደንብ በጥብቅ የተከለከለው ተግባር የግብይት አባላት አንዳንድ ደንበኞችን ከሌሎች ይልቅ ቅድሚያ መስጠት ወይም ማበላለጥ ነው። ሁሉም ሂሳቦች በትዕዛዝ አያያዝ መርሆዎች ቅደም ተከተል መሠረት ፍትሃዊ አያያዝ የማግኘት መብት አላቸው።

የግብይት አባላት ለሌላ የግብይት አባል ግዴታውን ላልፈጸመ ደንበኛ ግብይት መፈጸም የተከለከለ ነው። ለዚህ አላማ ሲባል የግብይት አባላት ግዴታቸውን ያልፈጸሙ በስራቸው ያሉ ደንበኞችን ዝርዝር መረጃ በየጊዜው ለገበያው እንዲልኩ ደንቡ ያስገድዳል። ይህም እነዚህ ደንበኞች ሌሎች የግብይት አባላትን በመጠቀም ግብይት እንዳይፈጽሙ ገበያው ቁጥጥር እንዲያደርግ ይረዳል። ገበያው ይህን ግዴታቸውን ያልተወጡ ደንበኞች ስም ለግብይት አባላት በሙሉ ያዘዋውራል ወይም እንዲያውቁት ያደርጋል።

# የገበያው የግብይት ስራዎች

የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ቅጽ መ ምዕራፍ 7 የገበያውን የግብይት አሰራር ያቋቁማል። ገበያው በሥራ ቀናት በሙሉ ለግብይት ክፍት ሲሆን የግብይት ሰዓት በምስራቅ አፍሪካ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 3:00 እስከከቀኑ 9:00 ነው።፣ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ድረስ ያለው ጊዜ የቅድመ ግብይት መክፈቻ ክፍለ ጊዜ ይባላል። ይህ ክፍለ ጊዜ ግብይት ከመጀመሩ በፊት ያለ ጊዜ ሲሆን በዚህ ክፍለ ጊዜ ደንበኞች በግብይት አባላት በኩል የግዥ እና የሽያጭ ትዕዛዝ የሚያስገቡበት ነው። ይህም ገበያው ከደንበኞች የሰበሰበውን ትዕዛዝ በማገናዘብ ትክክለኛው ዋጋ በአቅርቦት እና ፍላጎት መሰረት ብቻ እንዲወሰን የሚያደርግ ነው።

ከዚህ የቅድመ መክፈቻ ክፍለ ጊዜ በመቀጠል ግብይቱ ይከፈትና (ይጀመርና) እስከ ቀኑ 9:00 ሰዓት ድረስ ይቀጥላል። በዚህ ክፍለ ጊዜ ግብይቶች የሚዛመዱበት ነው። ግብይቱ በምስራቅ አፍሪካ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 9:00 ሰዓት ላይ ይቆማል። ከዚህ ሰዓት በኋላ እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ ምንም ዓይነት ግብይት ማከናወን አይቻልም። ይሁን እንጂ በልዩ ሁኔታ በባለሥልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በገበያው ውሳኔ፣ ወይም በባለሥልጣኑ ጥያቄ የግብይት ሰዓቱ ሊራዘም የሚችልበት ሁኔታ በደንቡ ተመልክቷል።

ሌላው በተዛማጅ ወገኖች መካከል የሚደረጉ ግብይቶችን በተመለከተ ሲሆን በነዚህ ወገኖች መካከል የሚደረግ ከፍተኛ መጠን ያላቸው የአክሲዮን ግብይቶች ከመደበኛው የግብይት ሂደት ውጪ ሊፈጸሙ የሚችሉ ሲሆን ከክፍያ ነፃ በሆነ መልኩ ይዘዋወራሉ። ይህን ለማድረግ የግብይት አባላት በነዚህ ወገኖች መካከል የሚደረግ ግብይትን አስቀድሞ ለገበያው ማሳወቅ እና ማስፈቀድ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ መልኩ በተዛማጅ ወገኖች መካከል የሚደረግ ግብይትን ገበያው መርምሮ እንዲፈቅድ በተለይ አንደኛው ኩባንያ በሌላው ኩባንያ ውስጥ ለቁጥጥር የሚያበቃ አክሲዮን መጠንወይም ድርሻ ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን፣ ወይም ሁለቱም ኩባንያዎች በአንድ ወይም ሁለቱም ወገኖች በተመሳሳይ ቁጥጥር ሥር መሆን ወይም አለመሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።
ሌላው በገበያው ደንብ የተካተተው የግብይት አሰራር ባለቤት ያልሆኑበትን አክሲዮን መሸጥ የተከለከለ መሆኑ ነው። በአንጻሩ የአክሲዮን የብድር ሽያጭ የተፈቀደ ሲሆን ገበያውን ሊያውክ ከሚችል አሰራር የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ በገበያው በየጊዜው በሚወጡ ሁኔታዎች እና በባለሥልጣኑ መመሪያዎች መሰረት የሚተገበሩ ናቸው።

# ቀጥተኛ የኤሌክትሮኒክስ ተሳትፎ

ምዕራፍ 8 ስለበይነ መረብ የግብይት መድረክ የሚደነግግ ሲሆን ይህም የዘመናዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች እጅግ አስፈላጊ ገጽታ ነው። ቀጥተኛ የኤሌክትሮኒክስ ተሳትፎ የሚሰጡ የግብይት አባላት የተወሰኑ ደህንነታቸው የተጠበቀ የበይነ መረብ ግንኙነቶችን፣ የትዕዛዝ አስተዳደር ስርዓቶችን እና ጠንካራ የመረጃ ደህንነትን መጠበቅ ሥርዓት ሊኖራቸው ይገባል። የበይነ መረብ የግብይት መድረክ ለማቋቋም የሚፈልግ የግብይት አባል ገበያውን በማስፈቀድ ደህንነቱ የተጠበቀ የኔትወርክ ግንኙነት ሊዘረጋ እና የራሱ የትዕዛዝ አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖረው ይገባል።

በዚህ የዲጅታል ሥርዓት ውስጥ ግብይት ለሚያከናውኑ ደንበኞች በገበያው የግብይት ሥርዓት እንደሚከናወኑ ሌሎች ግብይቶች ሁሉ የደንበኛህን እወቅ መስፈርቶች ተግባራዊ ይደረግባቸዋል።
የበይነ መረብ የግብይት መድረኮች የአደጋ አስተዳደር ድንጋጌዎች ባለብዙ-ደረጃ ማረጋገጫ፣ ሚስጥራዊ፣ ማጭበርበርን እና የሳይበር ወንጀልን የሚያስተዳድሩ ፖሊሲዎችን የያዙ መሆን አለባቸው። የደህንነት ጥሰቶች የገበያ ተዓማኒነትን አደጋ ላይ የሚጥሉ ከሆነ ገበያው የበይነ መረብ ግብይት መድረኩን እንዲዘጋ ሊያደርግ ይችላል።

# ለግብይቶች ክፍያ መፈጸም

ምዕራፍ 9 ወሳኝ የሆነውን ከግብይት በኋላ የሚመጣውን የርክብክብ እና ክፍያ ሂደትን ይመለከታል። ለእያንዳንዱ ርክክብ ክፍያዎችን መፈጸም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እና የገንዘብ ማስተላለፍ ሂደትን በአንድ ጊዜ ማካሄድ የሚያስችል መሰረታዊ መርህ ነው። መሰረቱ ርክብክብ እና ክፍያ ገበያው በሚወስነው ጊዜ ሰሌዳና መሰረት የሚፈጸም ቢሆንም በዚህ አኳኋን ያልተፈጸሙ ግብይቶች ሪፖርት እና ተገቢ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።

# የግብይት ሥነ-ምግባር

ሌላው የገበያው መተዳደሪያ ደንብ ቅጽ መ ክፍል 6 ዝርዝር የግብይት ሥነ-ምግባር መስፈርቶችን ያስቀምጣል። የተከለከሉ ተግባራት፣ ጆሮ ጠብ እና ከደንበኞች ቀድሞ ግብይት መፈጸም (ከደንበኛ ትዕዛዞች በፊት መገበያየት)፣ የገበያ ማጭበርበር፣ የውስጥ አዋቂ ግብይት፣ ለኮሚሽን ተብሎ የደንበኛ ሒሳቦች ላይ ተደጋጋሚ ግብይት መፈጸም ክልከላ እና የተለያዩ አታላይ የግብይት ዘይቤዎችን ያካትታሉ።

የደንቡ የውስጥ አዋቂ ግብይት ድንጋጌዎች የውስጥ ሰዎች በውስጥ መረጃ ላይ እንዳይነግዱ፣ እንደዚህ አይነት መረጃ በአግባቡ እንዳይገልጹ ወይም ሌሎች እንዲነግዱ እንዳያበረታቱ ይከለክላሉ። እነዚህ ድንጋጌዎች በኩባንያው ውስጥ ያሉ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ የውስጥ መረጃ ላለው ለማንኛውም ሰው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

# ግዴታዎችን አለመወጣት እና ኪሳራ

መሰረቱ ማንኛውም የግብይት አባል ከሌላ ከማንኛውም የካፒታል ገበያ ተዋንያን ጋር ባለው ግብይት መፈጸም የሚገባውን ክፍያ አለመፈጸም አይችልም የሚል ነው። ሆኖም የአንዳንድ የግብይት አባላት ግዴታቸውን መወጣት አለመቻል የሚያሳዝን ነገር ግን የማይቀር እውነታ ነው። ግዴታውን መወጣት ያልቻለ የግብይት አባል ይህንኑ ወዲያውኑ ለገበያው ማሳወቅ አለበት። ምዕራፍ 11 ታዲያ እንዲህ ያሉ ክስተቶች ሲፈጠሩ ገበያው ግዴታ አለመወጣትን ሊያውጅ እና አበዳሪዎችን ስብሰባ ለመጥራት፣ ሂሳቦችን ለመመርመር እና ጊዜያዊ አስተዳደር መሾምን ጨምሮ እርምጃዎችን ለመምከር ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል።
በቀጣይከኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ የመጨረሻ የሆነውን ቅጽ ሠ  በጥልቀትየምንዳስስ ይሆናል።